28ኛ ዓመት ቁጥር -5
28th Year No -5

ባህር ዳር ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም
Bahir Dar 4st day of July, 2024

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 240.12 Unit Price	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 214/2016 ዓ.ም	Regulation No. 214/2024
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የመንገድ ስራዎች ድርጅት ስያሜ ለውጥ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	The The Amhara National Regional State Revised Amhara Road Works Enterprise's Name Change, Council of Regional Government Regulation
ደንብ ቁጥር 214/2016 ዓ.ም	REGULATION NO. 214/2024
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የመንገድ ስራዎች ድርጅት ስያሜን ወደ ህብር ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ለመለወጥ የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO CHANGE THE NAME OF THE REVISED ROAD WORKS ENTERPRISE TO HIBIR CONSTRUCTION CORPORATION IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 170/2010 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣ ቢሆንም ስያሜውን ህብር ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን በሚል መቀየር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ድርጅቱ በምስራቅ አፍሪካ ተመራጭ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ለመሆን እንደ አንድ ቢዝነስ ተቋም ስያሜውን ማስተካከል የግድ በመሆኑና ከዚህ በፊት የነበረው ስያሜ የአንድን አካባቢ ስያሜ የያዘ በመሆኑ፤

የአማራ መንገድ ስራዎች እና የአብክመ ገጠር መንገድ ኤጀንሲ የስያሜ መቀራረብ ያላቸው ከመሆኑም በላይ የድርጅቱም አርማ ውስብስብ ሆኖ በደንበኞች በኩል ለመረዳት አዳጋች ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በክልሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 236/2008 ዓ.ም አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ::

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የመንገድ ስራዎች ድርጅት ስያሜ ለውጥ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 214/2016 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Whereas, although the Amhara National Regional State Road Works Enterprise Re-establishment, Council of Regional Government Regulation No. 170/2018 has been revised and issued, it has been found necessary to change its name to Hibir construction corporation;

Whereas, the Enterprise, to be prime road works contractor in the East Africa , it is necessary to adjust its name as a business institution since the existing name designates one particular locality;

Whereas, beyond having name resemblance between the Amhara Road Works Enterprise and the ANRS Rural Road Agency, the Enterprise's emblem is so complicated, it has been found difficult to understand it on part of costumers;

Now, Therefore, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 subs. Art. (7) of the Revised Regional Constitution and Art. 46 Sub Art. (1) letter number A. of the Regional State Enterprises Establishment, Organization, Management and Support-Provision Proclamation No. 236/2016, hereby issues this regulation.

1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amhara National Regional State Revised Amhara Road Works Enterprise's Name Change, Council of Regional Government Regulation No. 214/2024."

2. ማሻሻያ

ተሻሽሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 170/2010 ዓ.ም መሰረት የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት ተብሎ ሲጠራ የነበረው ከዚህ በኋላ "ህብር ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን" በሚል እንዲጠራ በዚህ ደንብ የስያሜ ለውጥ ተደርጎለታል።

3. ስለተሻሩና እና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት እንደገና መቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 170/2010 ዓ.ም አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 በዚህ ደንብ ተሽሮ።

2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

4. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም
አረጋ ከበደ
የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ-መስተዳድር

2. Amendment

The so-called the Amhara Road Works Enterprise, pursuant to the revised and issued Regulation No. 170/2018, has got its name change under this regulation and shall be hereinafter called "**Hibir Construction Corporation**".

3. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Amhara National Regional State Road Works Enterprise Re-Establishment, Council of Regional Government Regulation 170/2018 Art. 3 Sub. Art. 1 is hereby repealed by this Regulation.

2. No other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall be applicable with respect to the matters covered therein.

4. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its approval of this 4th July, 2024 by the Council of the Regional Government.

Done at Bahir Dar
This 4st day of July, 2024
Arega Kebede
Head of Government of the Amhara National Regional State